# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ሐምሌ 16 ቀን 2004 ዓ.ም

## በሙስሊም ኢትዮጵያውያን ላይ የሚደረገውን አፈናና ግድያ እናውግዝ

የወያኔ ዘረኛና ፀረ ኢትዮጵያ አገዛዝ በሙስሊም ኢትዮጵያውያን ላይ እየፈፀመ ያለውን አፈና፥ እስራትና ግድያ ኢሕአፓ ዳግም በጥብቅ ያወግዛል፡፡ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ወያኔን ማውገዝ ብቻ ሳይሆን ወገኖቻችን እያደረጉ ያሉትን ትግል በገቢር እንዲደግፍም ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

ባለፉት ሳምንታት ስድስት ዜጎች ሲገደሉ ከሺህ አምስት መቶ በላይ ደግሞ በወያኔ ታፍሰውታስረዋል፡፡ መዳረሻቸው ገና አልታወቀም፡፡ ሙስሊም ዜጎች እየታቃወሙ ያሉት ወያኔ በሃይማኖት ጉዳያቸው ጣልቃ እየገባ ማተራመሱንና ጭቆና ማካሄዱን ነው፡፡ ወያኔ ምዕመናኑን ወደ አንዋር መስጊድ እንዳይደርሱ አግዶ፤ የሴቶችን ልብስ እየገፈፈ፤ ዜጎችን እየደበደበ በመቶዎች የሚቆጠሩትንም አፍሶ ወስዷል፡፡ የወያኔ ባለሥልጣናት የሙስሊም ዜጎችን ተቃውሞ ፀረ ሰላም፥ በውጭ ኃይሎችና ተቃዋሚዎች የተጠነሰሰ አድርገው ለማቅረብ የሚጮሁትም ውድቅ መሆኑን ማስረገጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ዛሬ ከኢትዮጵያ የነገ ዕጣ ፈንታ አንፃር ይህ ተቃውሞ አንጂ የመለስ መሞት መዳን ቁልፉን ቦታ እንዳልያዘ መገንዘብም ተገቢ ነው፡፡ የሙስሊም ኢትዮጵያውያን ትግል መደገፍ. ያለበት ነውና ኢሕአፓ ሙሉ ድጋፉን ይሰጠዋል ፤ በቦታው ያሉትም አባላት ይህንን ድጋፍ ተግባራዊ ይዘት እንዲሰጡት መመሪያውን ካስተላለፈ ቆይቷል፡፡

በሙሰሊም ዜጎች እየተካሄደ ያለው ትግል ይዘቱና አንደምታው ሀገራዊ ነው፡፡ ለዚህም ነው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊደግፈው የሚገባው፡፡ አስተማሪ ተማሪ፥ የቢሮ ሠራተኛ ታክሲ ነጂ፥ ሴቶች ወንዶች አዛወንትና ወጣቶች ሁሉ በተቃዋሞ መነሳት አለባቸው፡፡ በዚህ መንገድ ነው የየካቲት 66 አብዮት የተካሄደውና ውጤት ሊያመጣ የቻለው፡፡ በሕዘብ ትብብር፥ በትግሉ ቀጣይነት፤ ዛሬም ቢሆን የሙስሊም ዜጎች ትግል የመላውን ኢትዮጵያዊ ድጋፍ ይፈልጋል፡፡ ያለው ሁኔታ፥ ለውጥን አዋላጅ ሊሆን የሚችል ነውናም ሁሉም ዜጋ ዋና ትኩረቱ ሙሰሊም ዜጎችንና ትግላቸውን መደገፍና ሕዘባዊ አመፅን ማጠናከር መሆን አለበት፡፡ ከወያኔ ለዉጥን መጠበቅ ከእባብ ዕንቁላል እርግብን መጠበቅ ነው፡፡

ለተባባረ ትግል እንነሳ!
አፈናና ግድያውን እንቃወም!


EPRP
P.O.Box 73337
Washington D.C. 20056
U.S.A
Tel. : (202) 291-4217
Fax : (202) 291-7645

EPRP
BP 22
Bois Colombes 92270
France

E-mail ESPIC@aol.com
Website: http://www.EPRP.com